# የደቀ መዝሙር አገልግሎትን እንዴት መጀመር ይቻላል

ZEKARIAS

- ማር 4:26-29 አንብቡ

ከዚያም እንዲህ አለ, “የእግዚአብሔር መንግሥት ይህን ትመስላለች፥ አንድ ሰው መሬት ላይ ዘር ይዘራል። ሰውየው ሌሊት ይተኛል ቀን ይነሳል፥ ነገር ግን እርሱ እንዴት እንደሆነ ሳያውቅ ያ ዘር በቅሎ ያድጋል፤ ምድርም ራስዋ፤ በመጀመሪያ ቡቃያውን፤ ቀጥሎ ዛላውን፤ ከዚያም በዛላው ላይ የጎመራ ፍሬን ታስገኛለች። ነገር ግን ፍሬው እንደበሰለም መከር በመድረሱ ፤ ሰውየው ወዲያው ማጭዱን አንስቶ አጨዳ ይጀምል።”

# የመንግስቱ እድገት ሂደት አራት መስኮች

ዘር መዝራት/
ወንጌል ማካፈል



ባዶ ቦታ መምረጥ/የአገልግሎት
ማሳችንን መለየት

የማይታይ ሰራተኛ/
መንፈስ ቅዱስ

የሚባዙ ቡድኖችን መገንባት

ደቀመዛሙርት ማድረግ
መጽሀፍ ቅዱስ ማጥናት



የሐዋሪያት ሥራ 2
ማህባረሰቦችን





# 1. ባደ ቦታ መምረጥና መሄድ

- ሂዱ = መሄድ
- ሮሜ 15፥20 ሌላው በጣለው መሠረት ላይ እንዳልገነባ ብዬ፤ ክርስቶስ ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዘወትር ምኞቴ ነበር።
- ተልዕኮ ያላት ቤተ ክርስቲያን ዓለምን ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትጠራ ሳትሆን ወደ ዓለም የምትሄድና ዓለምን የምትለውጥ ናት
- ለዓለም ጨውነቷን የምታሳይ ናት
- ለጨለመባት ዓለም ብርሃንን የምታሳይ ናት
- ወደ የት ነው መሄድ ያለብን?

# ወደ የት ነው መሄድ ያለብን?

- ወንጌል ሰምተው ወዳልዳኑ ሰዎች ማቴ 28፥18-20
  - እስቲ ጥቂት ቆም ብለን የግንኙነት መረባችንን እንመልከት
- በክርስቶስ አምነው ያልዳኑ ሰዎች ታውቃለህ?
  - በቤተሰቦችህ መካከል
  - ደኞች
  - ጎሬቤቶችህ
  - የስራ ባልደረቦች
  - ተማሪዎች
  - መዝግቡአቸው

- ወንጌል ወዳልደረሰበት ሰፈር ሐዋ 1፥8
  - ክርስቲያኖች የሌሉበት ሰፈር፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞን ታውቃላችሁ? መዝግቡ
  - በወንጌል ያልተደረሰ አካባቢ፣ ብሔረሰብ ታውቃላችሁ?
- ወደ ዓለም ሁሉ ማር 16፥16

# 1. ወንጌልን መስበክ

- ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ማር 16፡16
- ወንጌል ስለ ክርስቶስ ነው ሮሜ 1፡3-6
- 3ወንጌሉም ስለ ልጁ፤ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለሆነ፥ 4በቅድስና መንፈስ ደግሞ ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተገለጠው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 5በእርሱ በኩል ስለ ስሙ ከአሕዛብ ሁሉ መካከል ሰዎችን በእምነት አማካይነት ወደሚገኘው መታዘዝ ለመጥራት ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን። 6እናንተ ራሳችሁም ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሆኑ ከተጠሩት መካከል ናችሁ።
- ክርስቶስን ለሰዎች ማስተዋወቅ ነው
- ወንጌል ሥርጭት ላይ እንዴት ናችሁ?
- በአጥቢያችሁ በዓመት ምን ያህል አዳዲስ ሰዎች ጌታን ይቀበላሉ?

# ማን ይሰበክ? እንዴት?

- ሮሜ 10፥13-15 የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል። እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙት እንዴት ያምናሉ? ያለሰባኪ እንዴት ይሰማሉ? መልካሙን የምስራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደተጻፈ ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ
- በዚህ ክፍል ሰዎች እንዲድኑ የሚወድ እግዚአብሔር ከእኛ ምን እንደሚፈልግ እናያለን
  - ድነት
  - እምነት
  - መስማት = የእግዚአብሔርን ቃል
  - ሰባኪ
  - ላኪ

# 3. ደቀ-መዝሙር ማድረግ

- ደቀ-መዝሙር ማድረግ ብዙ ለቤተክርስቲያን የተሰጡ የመከሩ ሠራተኞችን የምናፈራበት ነው
- ወንጌልን መስበክ ምዕመናንን ወደ ቤተክርስቲያን ይጨምራል። ደቀ-መዝሙር ማድረግ ግን ምዕመናንን በቤተክርስቲያን ያበዛል።
- ደቀ-መዝሙር ማድረግ
  - ማስተማር (ቃሉን እንዲታዘዙ)
  - ማሰልጠን
  - መከታተል
  - ማሳደግ
  - መምራትን ያጠቃልላል

## ደቀመዛሙርት የመባዛት ሕይወት ነው



- ደቀ መዝሙርነት ላይ እንዴት ናችሁ?
- በቤተ ክርስቲያናችሁ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ለማድረግ ምን ምን ስልቶችን ትጠቀማላችሁ?

# እግዚአብሔር አንድ ነገር እንድንሠራ በታላቁ ተልዕኮው ሰጥቶናል፡፡
# ይህም ደቀ-መዝሙር እናደርግ ዘንድ፡፡



# 4. ቤተ ክርስቲያንን መትከል

- ተልዕኮውን ከኢየሱስ የተቀበለችው ቤተ ክርስቲያን ናት፤ ተልዕኮው እንዲቀጥል ቤተክርስቲያን በጽኑ መሠረት ላይ ልትተከል ይገባል

የመጀመሪያዋ ሞዴል ቤተ ክርስቲያን

- የሐዋሪያት ሥራ 2
- 42እነርሱም በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት፥ እንጀራውንም በመቍረስና በጸሎት ይተጉ ነበር። 43በሐዋርያት እጅ ብዙ ድንቅና ታምራት ይደረግ ስለ ነበር፥ ሰው ሁሉ ፍርሀት ዐደረበት። 44ያመኑት ሁሉ በአንድነት ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ የጋራ አደረጉ። 45ሀብታቸውንና ንብረታቸውንም እየሸጡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚያስፈልገውን ያህል ይሰጡት ነበር። 46በየዕለቱ በቤተ መቅደስ በአንድነት እየተገናኙ፥ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በቀና ልብ ይመገቡ ነበር፤ 47እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ፥ በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው፤ ጌታም የሚድኑትን በቍጥራቸው ላይ ዕለት በዕለት ይጨምር ነበር።

# የቡድን ውይይት

- ከመጀምሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት ባህሪ ትረዳላችሁ?

# ልንኮርጀው የሚገባ የመጀምሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ባህሪ

- ትምህርት
- ኅብረት
- እንጀራውን መቍረስ
- በጸሎት መትጋት
- ድንቅና ታምራት
- ይፈሩ ነበር
- ያላቸውን ሁሉ የጋራ ያደርጉ ነበር
- በየዕለቱ በቤተ መቅደስ ይገናኙ ነበር
- በደስታ ነበሩ
- ቀና ልብ ነበራቸው
- እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር
- ሞገስ ነበራቸው
- የሚድኑት በቍጥራቸው ላይ ዕለት በዕለት ይጨምሩ ነበር

# 5. መንፈስ ቅዱስ = የማይታይ ሰራተኛ

1. መንፈስ ቅዱስ የማይታይ ሰራተኛ ነው

- በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የክርሰትና ህይወት ዋነኛ ነገር ነዉ
- ሐዋርያት ምንም እንኳን ከጌታ ጋር በሦስት ዓመት ምድራዊ አገልግሎት አብረዉት ቢኖሩም የጌታችንን ታላቅ ተልዕኮ ለመፈጸም ዝግጁ አልነበሩም ፤ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ገና አልተሞሉም ነበርና፡፡
- ሐዋ. 1፡8 ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።
- ኢየሱስ እርሱ ካደረገዉ የበለጠ እንደምናደርግ ተስፋ ሰጥቶናል(ዮሐ. 14፡12-14
- የሚያስገርመዉ ግን ብዙ ክርስቲያኖች እንዴት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንደሚችሉእና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚመላለሱ አያዉቁም

# መንፈስ ቅዱስ ለምን መጣ?

- ክርስቶስን ለማክበር (ዮሐ.16፡7፣13፣14)
- ወደ እውነት ሁሉ ሊመራን (ዮሐ. 16፡13)
- ክርስቶስን እንድናውቅና ለእርሱ እንድንኖር ኃይል ሊሰጠን

. የተትረፈረፈ ሕይወት እንድንኖር ለማስቻል ዮሐ.7፡37-39

. ለመመስከር ሐዋ.1፡8

. ውጤታማ ጸሎት ለመጸለይ ሮሜ 8፡26

# ለምንድን ነዉ አብዛኛዉ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላው?

- ከእዉቀት ማነስ የተነሳ ፤ ዕውቀት ማጣት ወደ እምነት ማጣት ያደርሳል
- ከእምነት ማጣት የተነሳ

- ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ይፈሩታል እንጂ አያምኑትም
- አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ምክንያታዊ ያልሆነ የፍቅሩን ስፋት ይጠራጠራሉ
- እግዚአብሔር ለነሱ ያለዉን ዓላማ ምን ያህል አስደናቅ መሆኑን አልተገነዘቡም (ማቴ.6፡33)

# በመንፈስ ቅዱስ የምትሞላው እንዴት ነው?

1. በእምነት

- ክርስቲያን የሆንከው በእምነት ነው (ኤፌ 2፡8)
- እንዲሁ በመንፈስ የምትሞላው በእምነት ነው (ቆላ 2፡6)
- አንዴ የተሰጠህን ነገር እግዚአብሔር እንዲሰጥህ መለመን የለብህም

2. በፋቃደኝነት

- ልብህን ለማዘጋጀት የሚረዱ ቅድመ ሁኔታዎችን በማወቅ
- ጌታን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት ለመኖር መፈለግ (ማቴ 5፡6)
- ኃጢአትህን መናዘዝ
- ራስህን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን

# ስኬታማ ምስክርነት

# ምስክርነት

- ሉቃ 24፥44-49
- 44እርሱም፣ “ከእናንተ ጋር በነበርሁበት ጊዜ፣ ‘በሙሴ ሕግ፣ በነቢያትና በመዝሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል’ ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው” አላቸው።
- 45በዚህ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያስተውሉ አእምሯቸውን ከፈተላቸው፤ 46እንዲህም አላቸው፤ “ ‘እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፤ ክርስቶስ መከራን ይቀበላል፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፤ 47ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ለሕዝቦች ሁሉ ንስሓና የኀጢአት ስርየት በስሙ ይሰበካል፤’ 48እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ። 49እኔም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኀይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቈዩ።”
- ሐዋ 1:8

# የወንጌል ምስክርነት

- ክርክር አይደለም
- ጭቅጭቅ አይደለም
- በንግግር ሰውን ማስደመም አይደለም
- ሰውን ማበሳጨትም አይደለም
- ምክንያት በመደርደር ሰውን መርታት አይደለም

- የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ ነው

# የትምህርቱ ዓላማ፡- የስኬታማ ምስክርነትን ምንነት ማስረዳት ነዉ፡፡

- **የትምህርቱ ግብ፡-** ይህ ትምህርት በመንፈስ ቅዱስ ለሚደረግ ምስክርነት ከግል ዝግጅት ጋር የተያያዙትን ደረጃዎች ለመረዳትና በተግባር ለማዋል ይጠቅማል፡፡
- ስኬታማ ምስክርነት በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ለመመስከር እርምጃ ከመውሰድ ጋር የተያያዙ ደረጃዎችን ለመረዳትና በተግባር ለማዋል ይጠቅማል

The picture can't be displayed.

# ስኬታማ ምስክርነት

- አንድ ምስክርነት ስኬታማ/ውጤታማ ነው የሚባለዉ፡- በራስ አነሳሽነት የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት በመታገዝ መናገርና ውጤቱን ግን ለእግዚአብሔር መተው ሲቻል ነዉ፡፡
- በራስ አነሳሽነት
- የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት
- መናገር

ይህ ምዕራፍ ሁለት ክፍል አለዉ

1. የግል ዝግጅት
2. ተግባራዊ እርምጃ

# 1. የግል ዝግጅት

## 1.1 <u>በክርስቶስ አምነህ የዳንክበትን እውቀት አጥብቀህ ያዝ</u>

- ጥሩ ሰዉ ፣ ግብረገባዊ ሰዉ ፣ ኃይማኖተኛ ወይም የቤ/ክ አባል ብቻ መሆን አይበቃም

❖ክስቶስን በእምነት መቀበል ኤፌ 2፥8

❖ለክርሰቶስ መሰጠት፤ ይህም ሁለንተናን ፣ አዕምሮን፣ ስሜቶችንና ፈቃድን ያጠቃልላል

# 1.2 ያልተናዘዝከዉ ኃጢአት በህይወትህ እንደሌለ አረጋግጥ

- ደስተኛና ፍሬያማ ሆነዉ ነገር ግን የማይታዘዙ ክርስቲያኖች የሉም ፡፡
- ኃጢአት ደስተኛ ክርስቲያን ከመሆን ያግደናል ፤ እግዚአብሐርንም ያሳዝነዋል ስለዚህ ኃጢአታችንን መናዘዝ ይኖርብናል፡፡
- 1ዮሐ. 1፡9


መንፈሳዊ
ሰዉ
አንዴት
መንፈሳዊ አተነፋፈስ
ስጋዊ ክርስቲያን
ፍጥረታዊ ሰዉ

- መዝ 66፡18 በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን ጌታ አይሰማኝም ነበር።
- ኃጢአተኛነታችንን አለማመናችን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረታችንን ይጎዳል
- እዉነተኛ ንስሃ የሚከተሉትን ያጠቃልላል

1. ያደረግነዉ ወይም ያሰብነዉ ትክክል እንዳልሆነ ከእግዚአብሔር ጋር መስማማት፡፡ ለኃጢአታችንም ምክንያት ከማቅረብ በመታቀብ መሳሳታችንን ማመን፡፡

# 1.3. በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ

- ሰው በመንፈስ ቅዱስ ሊሞላ የሚችለዉ የመንፈስ ቅዱስን ማንነትና የመጣበትን ተልዕኮ ሲረዳ ፣ ህይወቱን እንዲመራና እንዲቆጣጠር ሲፈቅድለት ነው፡፡
- ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በእምነት በፈቃደኝነት ነው/ መንፈሳዊ አተነፋፈስን በመለማመድ ነው
- ሐዋ 1፡8

# 1.4. በክርስቶስ ያለህን እምነት ለማካፍል ተዘጋጅ

1ጴጥ. 3፥15-16

*ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።*

*በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን የሚሳደቡ ሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያሙበት ነገር እንዲያፍሩ በጎ ሕሊና ይኑራችሁ።*

ትኩረት የሚሹ 3 መሠረታዊ ነጥቦች

1. የልብ ዝግጅት
2. ስልጠና
3. እምነታችንን ስናካፍል ኢየሱስ ከእኛ ጋር መሆኑን ማወቅ ማቴ. 28፡20

# 2. ተግባራዊ እርምጃ

## 2.1. ጸልይ

- እስቲ ጥቂት የጸሎት ጊዜ ውሰድና እግዚአብሔር በልብህ የሚያመጣቸውን ከ5-10 ሰው ስም ዝርዝር ለጸሎት በማስታወሻህ ያዝ፤ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲመራ መጸለይ ጀምር
- ዮሐ. 6፡44 የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥
- ለሰዎች መዳን ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኖችም ስለመንፈሳዊ እድገታቸዉ ጸልይ

- በክርስቶስ አምነው ያልዳኑ ሰዎች ታውቃለህ? የግንኙነት መረብህን ፈትሽ
    - በቤተሰቦችህ መካከል
    - ጓደኞች
    - ጎሬቤቶችህ
    - የስራ ባልደረቦች
    - ተማሪዎች
    - መዝግቡአቸው

# 2.2 ወደ ሰዎች ሂድ

- ማር. 4፥19 የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፥ የማያፈራም ይሆናል።
- እንድንሄድ እታዘናል ማቴ 28፥18-20
- የምስክርነት ስኬታማነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እርምጃ መውሰድና ውጤቱን ለእግዚአብሔር መተው ነው
- ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ንቁ ሁን

# 2.3. ስለኢየሱስ ክርስቶስ ተናገር

- ቆላ. 1፥28 *እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው።*
- ስለ አዳኙ ስትናገር ብዙዎች እርሱን ለመቀበል ዝግጁ እንደሆኑ ታያለህ
- ክርክሮችን አስወግደህ ወንጌልን በፍቅር አቅርብ

# 2.4.እግዚአብሔር እንደሚጠቀምብህ  እመን

- የሐ.4፡10-15
- የዘመናችን ትልቁ ውሸት ሰዎች እግዚአብሔርን ማወቅ እንደማይፈልጉ አድርጎ ማቅረብ  ሲሆን እዉነቱ ግን ሰዎች እግዚአብሔርን መራባቸዉ ነው፡፡

# ውጤታማ ምስክርነት

- አንድ  ምስክርነት ውጤታማ ነው የሚባለዉ፡- በራስ አነሳሽነት የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት በመታገዝ መናገርና ውጤቱን ግን ለእግዚአብሔር መተው ሲቻል ነዉ፡፡
- በራስ አነሳሽነት
- የክርስቶስ ኢየሱስን አዳኝነት
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት በመታገዝ መናገርና
- ውጤቱን ግን ለእግዚአብሔር መተው ነዉ፡፡

# ውጤታማ ምስክርነት

1. ክርስቲያን መሆንህን አረጋግጥ
2. በሕይወትህ ያልተናዘዝከው ኃጢአት
3. በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ
4. እምነትህን ለማካፈል ተዘጋጅ
5. ጸልይ
6. ወደ ሰዎች ሂድ
7. ስለ ኢየሱስ ተናገር
8. ውጤት ጠብቅ